# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 330 ነሃሴ 30 2006 ገጽ


እየተካሄደ ያለው የህወሓት የጅምላ ስልጠና ለኢ-መደበኛ ድርጅቶች መስፋፋት ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል። የግንቦት 7 አባላትና ደጋፊዎች እነዚህን ስልጠናዎች የግንቦት 7 ሴሎችን ለማደራጀት እንዲጠቀሙበት እንመክራለን። ግንቦት 7 በኢትዮጵያ ወጣት የፈጠራ ችሎታ ላይ እምነት አለው። የኢትዮጵያ ወጣት አደንቁሮ ሊቀብረው የመጣውን ስልጠና ህወሓትን ለመቅበሪያነት እንደሚጠቀምበት የግንቦት 7 እምነት ነው።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የግንቦት 7 የፍትህ፤ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ አለማቀፍ ህዝባዊ ስብሰባዎች ተሳካ ሁኔታ ተካሄዱ

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በመላው ዓለም ከሚገኙ አባላት፣ ደጋፊዎቹና በአጠቃላይ ከኢትዮጵያውያን ጋር በወቅታዊ አገራዊ ሁኔታዎች ላይ ለመመካከር በ 30 ታላላቅ ከተሞች ካሰናዳቸው ህዝባዊ ስብሰባዎች መካከል አብዛኞቹ ባሳለፍነው እሁድ አገስት 31 ቀን 2014 ኢ.ም በድምቀ በመካሄዳቸውን ዘጋቢዎቻችን ያደረሱን መረጃ ያመለክታል። በእነዚህ በአምስት አህጉራት፤ በዘጠኝ አገሮችና 17 ከተሞች በተካሄዱት ህዝባዊ ስብሰባዎች ላይ ኢትዮጵያውያን በነቂስ በመውጣት የታደሙበት እንደነበር ያደረሱን ዘጋቢዎቻችን አገር ወዳድ ኢትዮጵያኑ ከንቅናቄው ከፍተኛ አመራሮች ጋር ሰፊ አገራዊ ውይይት ያካሄዱበት እንደነበር ለማወቅ ተችሏል። ኢትዮጵያውያን በዘር በሃይማኖት በጎሳ ሳይለያዩ በአንድነት በመሰባሰብ በአገራቸው ጉዳይ ላይ በሰፊው የመከሩበት፤ ኢትዮጵያዊነት እጅግ አምሮና አሸብርቆ የታየበት በአይነቱ ልዩ የሆነ ህዝባዊ ስብሰባ እንደነበር በርካቶች ምስክርነት እንደሰጡም ዘጋቢዎቻችንን አመልክተዋል። የንቅናቄው ከፍተኛ አመራሮች በክብር እንግድነት በተገኙባቸውና በስካይፒ በመሩዋቸው ህዝባዊ ስብሰባዎች ላይ ከተሳታፊው የደመቀ አቀባበል እንደተደረገላቸውም ለማወቅ የተቻለ ሲሆን አመራሮቹ ከተሳታፊዎች ለቀረበላቸው በርካታ አገራዊ ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥተዋል። በህዝባዊ ስብሰባዎቹ ላይ በክብር እንግድነት የተገኙት በአሜሪካ የዋሽንግተን ዲሲ ግዛት የንቅናቄው ዋና ሊቀመንበር ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ፤ በአትላንታ አቶ ነአምን ዘለቀ፤ በቦስተን የንቅናቄው የህዝብ ግንኙነት ተጠሪ አቶ ኤፍሬም ማዴቦ፤ በካናዳ ቶሮንቶ አቶ አንድነት ሃይሉ፤ በጀርመን ሙኒክ አቶ ብዙነህ ጽጌ በኖርዌይ ኦስሎ የንቅናቄው ም/ ሊቀመንበር አቶ አበበ ቦጋለ ሲሆኑ በስካፒ የተደረጉትን ስብሰባዎች የመሩት በደቡብ አፍሪቃ ደርባን፡ ጆሃንስበርግና ፔሪኒንገን ዶ/ር ታደሰ ብሩ፤ በሩስተምበርግ አቶ ቸኮል ጌታሁንና በአውስትራሊያ ፐርዝ የተካሄደውን አቶ ብዙነህ ጽጌ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል።

በህዝባዊ ስብሰባዎች ላይ በየመን የፀጥታ ሃይሎች ተይዘው አለማቀፍ ህግን በጣሰ አካሄድ ለጉጅሌዎቹ ተላልፈው የተሰጡት የንቅናቄው ዋና ፀሐፊ የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ሥራዎች በምስልና በቪዲዮ ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## በቀጣዮቹ የግንቦት 7 ህዝባዊ ስብሰባዎች ኢትዮጵያውያን በነቂስ በመውጣት እንደሚሳተፉባቸው ይጠበቃል

ግንቦት 7 የፍትህ፤ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ባሳለፍነው ቅዳሜ፤ እሁድና ሰኞ በአሜሪካ የተለያዩ ግዛቶች የተካሄዱትን ጨምሮ በደ.አፍሪካ፣ በኖርዌይ፡ በጀርመን፤ በካናዳ፡ በአውስትራሊያ፡ ፊንላንድ፡ በኒውዝላንድና በደ. ኮርያ ስኬታማ ህዝባዊ ስብሰባዎችን ማካሄዱን መዘገባችን ይታወሳል። ላንች ነው ኢትዮጵያ! የሚል ስያሜ በተሰጠው በዚህ ህዝባዊ ስብሰባ ኢትዮጵያውያኑ በወቅታዊ አገራዊ ጉዳዮችና ንቅናቄው ወደ ፊት ሊወስድ ባሰባቸው ዕቅዶች ዙሪያ ሰፊ ውይይት ማድረጋቸውን ተዘግቧል። በየመድረኩም ለወጣቶች፡ ለሴቶች ባጠቃላይ ለኢትዮጵያ ህዝብና ለመከላከያ ሰራዊቱ የተቀላቀሉን ጥሪ ቀርቧል። በቀጣይ ቀናት በሚካሄዱት ህዝባዊ ስብሰባዎችም በሌሎች አገራት እንደታየው ሁሉ በየ አገራቱ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በነቂስ በመውጣት እንደሚታደሙባቸውና ከንቅናቄው ከፍተኛ አመራሮች ጋር በአገራቸው ወቅታዊ ጉዳይ ላይ ሰፊ ምክክር እንደሚያደርጉ ይጠበቃል። በዚህ በያዝነው ሳምንት በሴፕቴንበር 6 በአሜሪካ በሎሳንጀለስ ግዛት፤ በአውሮጳ በእንግሊዟ ለንደንና በስዊድን እስቶኮልም እንዲሁም በሴፕቴንበር 7 በሳንቲያጎ አሜሪካና በሜልቦርን አውስትራሊያ ህዝባዊ ስብሰባዎች በድምቀት እንደሚካሄዱ ይጠበቃል። የህዝባዊ ስብሰባዎች ቅድመ ዝግጅት ተጠናቆ ኢትዮጵያውያን እየተጠበቁ እንደሚገኙም ከየ አገራቱ አስተባባሪ ኮሚቴዎች ያገኘነው መረጃ ያመለክታል። ግንቦት 7 የፍትህ፤ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በያዝነው ሳምንት መጨረሻ በሚካሄዱት ህዝባዊ ስብሰባዎች ላይ በየ አገራት የሚገኙ ኢትዮጵያውያን እንዲገኙ በድጋሚ ጥሪውን ያቀርባል።

## ወያኔ በተማሪዎች ላይ የኃይል እርምጃ ሊወሰድ እንደሚችል መነገሩ ስልጠናዉን ዉጥረት አልብሶታል

የጉጅሌው ወያኔ በስልጠና ተቋማቱ እየደረሰበት ያለውን ተቃውሞ በሃይል ለማብረድ በተማሪዎች ላይ እርምጃ ሊወሰድ ይችላል መባሉን ተከትሎ በየተቋማቱ ውጥረት መንገሱን ምንጮቻችን አመለከቱ። በየስልጠና ተቋማቱ የተለዩ ጥያቄዎችን፡ አስተያየቶችንና ተቃውሞዎችን በሚያቀርቡ ተማሪዎች በጉጅሌው ቅጥረኛ በደህንነቶች ልዩ ክትትል እየተደረገባቸው እንደሚገኝም ለማወቅ ተችሏል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በሃይማኖት አክራሪነት እና በአሸባሪነት ዙሪያ ላይ የተደረጉ ውይይቶች ምንም አይነት መግባባት ያልታየባቸው እና ከጉጅሌው ቅጥረኛ አሰልጣኞች ሲነሱ የነበሩት ሃሳቦች በሃይማኖቶች መካከል ያለውን አንድነትና ፍቅር የሚያደፈርሱ መርዞች እንደነበሩና እንደተለመደው በውጪ በስደት የሚኖሩ የሃይማኖት አባቶችን ከመዝለፍ እና ከመወንጀል አንስቶ እስከ ተቃዋሚነት መፈረጅን ያጠቃልለሉ እንደነበር ምንጮቻችን አመልክተዋል። ተማሪዎቹ በሃይማኖቶች ዙሪያ ከአሰልጣኝ ካድሬዎች የሚሰጠውን ንግግር በማጉረምርምና በተቃውሞ እንደማይቀበሉት መግለፃቸው ታውቋል።

በየስልጠና ተቋማቱ የተማሪዎች ተቃውም ያላማረው የጉጅሌው ወያኔ በርካታ ቅጥረኛ የፖሊስ እና የደህንነት ሃይሎችን በተማሪዎች መሃል እና በግቢው ውስጥ በማፍሰስ ተማሪዎች እንዲሸማቀቁ እና እንዲፈሩ በማድረግ ላይ መሆኑን የገለጹት ምንጮቻችን የተለየ ጥያቂዎች እና አስተያየቶች በሚያቀርቡ ተማሪዎች ላይ ከየስልጠናው እየተጠሩ ማስጠንቀቂያ እየተሰጣቸው እንደሚገኝ ታውቋል።

## የኢህአዴግ አባላት በድርጅታቸው ላይ ጥያቄዎችን ማንሳት ቀጥለዋል

በአዲስ አበባ በተለያዩ ክፍለከተሞች በመካሄድ ላይ ባለው የኢህአዴግ አባላት ስብሰባ ፣ አባላቱ ዛሬም በርካታ ጥያቄዎችን ሲጠይቁ መዋላቸውን ከውስጥ ምንጮች የተገኘው መረጃ ያመለክታል። ዛሬ ከሰዓት በኋላ በአባላቱ ከተነሱት ጥያቄዎች መካከል፡- " የኢትዮጵና የኤርትራ ህዝቦች የማይነጣጠሉ የአንድ ሃገር ዜጎች ሆነው ሳለ በመሪዎች አለመግባባትና ሽኩቻ በመለያየታቸው እስከዛሬ ድረስ እየተላቀሱ ይገኛሉ፤ ይህም የሆነው በኢህአዴግም አስተዋፆ ጭምር ነው፤ አሁንም ቢሆን ከኛ ጋር መስማማት ከፈለጉ በራችን ክፍት ነው የምትሉት ከልባችሁ ነወይ?" የሚለው ጥያቄ ሰፊ ሰአት ወስዶ ማከራከሩ ታውቋል።

በሃይማት አክራሪነት ጉዳይ ለተነሱት ጥያቄዎች ደግሞ " ሰማያዊ ፓርቲ በአዲስ አበባ ሰልፍ በጠራበት ጊዜ ሰልፈኛው መስኪድ አካባቢ ሲደርስ ሙሉ ለሙሉ ለጸሎት ወደ መስኪድ እንደገባ አረጋግጠናል፤ ስለሆነም" መንግስት ሁሉንም ሚዲያዎች እንደጥፋተኛ ቆጥሮ ጋዜጦችና መጽሔቶችን እንዳለ ከገበያ ማስወጣቱ እኛ አባሎቹ የኢህአዴግን ክፍተት የምናውቅበት መንገድ ተዘግቷል፤ ኢህአዴግ ለስራ አጥ ዜጎች የስራ ዕድል እፈጥራለሁ እያለ በአንፃሩ ግን የስራ ዕድል የሚፈጠርላቸው ዜጎች በአባልነት ላይ የተመረኮዘ ለምን ይሆናል?

( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ተማሪዎች ዘንድሮም ለአባይ ግድብ ማሰሪያ ገንዝብ እንዲያዋጡ እየተገደዱ ነዉ

ኢትዮጵያ ዉስጥ ምንም ነገር ለማድረግ ባነገበዉ ጠመንጃና በጉልበቱ ብቻ የሚተማመነዉ የወያኔ አገዛዝ አዲሱን የትምህርት ዘመን መጀመር በተስፋ የሚጠባበቁትን ተማሪዎች ለአባይ ግድብ ማሰሪያ ገንዘብ አምጡ በሚል ጥያቄ እያስደነገጠ መሆኑን ዘጋቢዎቻችን በላኩልን ዜና ገለጹ። መጪውን የትምህርት ዘመን ለመጀመር የሚያስችል ምዝገባ ለማካሄድ በየትምህርት ቤታቸዉ የተገኙ ተማሪዎች ለአባይ ግድብ ገንዘብ የማያዋጡ ከሆነ እንኳን ትምህርት መጀመር መመዝገብም እንደማይችሉ በወያኔ ካድሬዎች እየተነገራቸዉ ነዉ።

ተማሪዎቹ በነፍስ ወከፍ 120 ብር የማይከፍሉ ከሆነ ምዝገባ እንደማያካሂዱ እንደተነገራቸው ለኢሳት እንደተነገራቸው ገልጸዋል። ሁለት እና ከዚያ በላይ ልጆች ያላቸው ወላጆች በቤተሰብ ደረጃ ሳይሆን በእያንዳንዱ ልጅ ስም የመክፈል ግዴታ ጥሎባቸዋል። አንዳንድ ተማሪዎች በእያመቱ ለአባይ ግድብ እየተባለ የምንከፍለው ክፍያ አግባብ አይደለም በማለት አስተያየታቸውን ለኢሳት ዘጋቢ ገልጸዋል። ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ወጣቱን ለማደንቆር ያለመው ስልጠና ህወሓትን ለመቅበሪያነት ይዋል !

ህወሓት፣ ከሶስት መቶ ሺህ በላይ የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎችን በየቦታው ሰብስቦ እያሰለጠነ ነው። ይህ ሲያልቅ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ስልጠና ይቀጥላል ተብሏል። በድምሩ ወደ ግማሽ ሚሊዮን የሚጠጋ ወጣት አንድ አይነት ሰነድ አንብቦ ለ2007 ትምህርት ይዘጋጃል ማለት ነው። ስልጠናው ወደ መንግሥት ሠራተኞችና ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎችም ይስፋፋል ተብሎ ይገመታል።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በዚህ ሥልጠና ላይ ያለውን እይታ በነሐሴ 16 ቀን 2006 ዓም ቁጥር 328 ርዕሰ አንቀጹ መግለጹ ይታወሳል። ግንቦት 7 የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በወያኔ ስልጠናዎች ላይ ተቃውሞ ለማሰማት መድፈራቸው ወጣቱ ለለውጥ የተዘጋጀ እንደሆነ አመላካች መሆኑን ተገንዝቦ ይህ የለውጥ ፍላጎት በድርጅት እንዲታገዝ ወጣቱ በትናንሽ ሕዋሶች ራሱን እንዲያደራጅ መክሯል። ሆኖም ግን ህወሓት ለስልጠናው የሰጠው ትኩረት ቀድሞ ከታሰበው በላይ በመሆኑ ንቅናቄዓችን በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ እንደገና ሊመለስበት ወስኗል።

ህወሓት፣ ይህንን ያህል መጠነ ሰፊ ስልጠና ማድረግ ለምን አስፈለገው? የዲሞክራሲ ኃይሎችስ ይህንን ስልጠና እንዴት ለራሳቸው ጥቅም ሊያውሉት ይችላሉ?

ህወሓት ይህንን ትርጉም የለሽ ስልጠና በአሁኑ ሰዓት ለመስጠት የፈለገበትን በርካታ ምክንያቶች ማቅረብ ቢቻልም የሚከተሉት ሁለቱ ግን ዋነኛዎቹ ናቸው ብለን እናምናለን።

አንደኛውና ዋነኛው ምክንያት ህወሓት የተከታዮች ድርቅ የደረሰበት መሆኑ አድርባይ መሪዎቹን ማሳሰቡ ነው። በሚሊዮን ይቆጠራሉ የሚባሉት የኢህአዴግ አባላት ልባቸው ከህወሓት ጋር አለመሆኑ ግልጽ እየሆነ መጥቷል። በተለይ ደግሞ በተላላኪዎቹ ብአዴን፣ ኦህዴድ እና ደህዴግ የተሰባሰቡ አባላት በግልጽ ህወሓትን መቃወም እየጀመሩ ነው። ህወሓት የራሱን መጥፊያ እያደራጀ መሆኑ የተሰማው በመሆኑ አዳዲስ “ምዕመናንን” ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አካባቢ መመልመል ይፈልጋል። የመንግሥት ንብረትና መዋቅር ለፓርቲ ስልጠና የሚጠቀም በመሆኑ ከብዛት የሚገኝ ትንሽም ቢሆን ጥቅም የሚያገኝ ከሆነ የወጭው ጉዳይ ህወሓትን አያሳስበውም። ስለሆነም ይህ ስልጠና በተቻለ መጠን ብዛት ያላቸዉን የተማተሩ ወጣቶች በአድርባይነት ለህወሓት ማሰለፍን አላማዉ አድርጎ የተነሳ ስልጠና ነዉ። ሁለተኛው አቢይ ምክንያት ደግሞ ህወሓት ለኢትዮጵያ ወጣት ለማስተላለፍ የፈለገው መልዕክት ወደ እያንዳንዱ የዩኒቨርስቲ ተማሪ ጆሮ መድረሱን ማረጋገጥ መፈለጉ ነው። መልዕክቱም “ሜዳ ውስጥ ያለሁት ተጫዋች እኔ ብቻ ነኝ። ለሚቀጥሉት አርባና አምሳ ዓመታትም እኔን የሚገዳደረኝ አይኖርም፤ ስለሆነም የኢትዮጵያ ወጣት ሆይ ለለውጥ ያለህ ተስፋ ከንቱ ነው። አርፈህ ቁጭ ብለህ ተገዛ” የሚል መልክት ነው።

ስልጠናዎቹ ከላይ የተጠቀሱትን ሁለት ዓላማዎችን በሚገባ ማስፈፀም ይችላሉ ብሎ መገመት ከባድ ነው። የስልጠናው ይዘት እጅግ የወረደ እና የሰልጣኞቹን ብስለት ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ መሆኑ ስልጠናውን ምፀት የበዛበት አድርጎታል፤ አሰልጣኞቹንም ትዝብት ውስጥ ጥሏቸዋል። የስልጠናዎቹ ጽሁፎች (ማንዋሎች) ይዘት ደግሞ የአዘጋጆቹ የእውቀት ማነስ ምን ያህል አሳሳቢ ደረጃ ላይ ያለ መሆኑ ለተማሪዎቹ ተጨባጭ ማስረጃዎች ሆነውላቸዋል። በአጠቃላይ ስልጠናው ለአሰልጣኝ ካድሬዎች ያልተዘጋጁበት ፈተና ደቅኖባቸዋል። የኢትዮጵያ ወጣት ሲሞሉት የሚሞላ ባዶ ጋን አለመሆኑን እያዩት ነው። ወጣቶች ጠጣር ጥያቄዎችን ያነሱባቸዋል፤ አሰልጣኖች እነዚህ ጥያቄዎች እንዴት መመለስ እንዳለባቸው ስለማያውቁ ይደናበራሉ። መልስ ሲጠፋ ቁጣ፣ ዛቻና ማስፈራሪያ ይከተላል።

ይህም ሆኖ እነዚህ ስልጠናዎች ለህወሓት ምንም ውጤት አያስገኙም ብሎ ማለፍ አይቻልም። የስልጠናዎቹ ውጤት የሚወሰነው ግን የኢትዮጵያ ወጣት ከህወሓት ውጭ ለሚመጣ መረጃ ባለው ቅርበት መጠን ነው። ሁሉም የመረጃ ምንጮች ተዘግተውበት የህወሓትን የእድገትና የሰላም መዝሙር ሲሰማ ለኖረ ሰው በስልጠናው የሚሰጡ ባዶ ፕሮፖጋንዳዎችን የመቃወሚያ ምክንያት አይኖረውም። ለተለያዩ የመረጃ ምንጮች ቅርበት ያለው ወጣት ግን የህወሓት መዝሙር ከግራዚያኒ የእድገትና የሰላም መዝሙር የተለየ አለመሆኑን ይረዳል። በፋሺስት ወረራ ወቅት ግራዚያኒም ኢትዮጵያን በመንገድና በህንፃ እየገነባሁ ነው፤ በጥቂት ዓመታት ውስጥ አውሮፓ የደረሰችበት ደረጃ ላይ አደርሳታለሁ ይል እንደነበር ይታወሳል።

የህወሓትን ኢትዮጵያን ለአርባና አምሳ ዓመታት የመግዛት እቅድን ወጣቱ ምክንያታዊ ነው ብሎ ይቀበላል? የራሱን አፋኝ ህጎች አክብረው እየተፍጨረጨሩ ያሉ ተቀናቃኖቹን እንኳን በእንጭጩ እየደፈጠጠ ያለ ሥርዓት “ኃላፊነት የሚሸከም አጣሁ” የሚለው ሰበቡ በወጣቱ ዘንድ ምን ያህል ተቀባይነት ይኖረዋል? በግንቦት 7 እምነት ይኸኛው የስልጠና ዓላማ ሊሳካ የሚችለው በዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ድክመት ብቻ ነው። ዘረኛውንና ዘራፊውን ወያኔ መጣል ብቻ ሳይሆን ከወያኔ በኋላ ፍትህ፣ እኩልነትና ብልጽግና የሚሰፍኑበትን ስትራቴጂ ያዘጋጀና ለስትራቴጂዉ ክንዉንራሱን ያዘጋጀ ድርጅት መኖሩን የኢትዮጵያ ወጣት ማወቅ ይኖርበታል። ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ከሌሎች ዲሞክራሲያዊ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ኢትዮጵያን ወደ ነፃነት፣ እኩልነትና ብልጽግና ጎዳና ለማስገባት እየታገለ መሆኑን ሁሉም ወጣት ሊገነዘብ ይገባል። ይህ ግንዛቤ ካለ የኢትዮጵያ ወጣት ለእብርተኛው፣ ዘረኛው፣ ሙሰኛውና ከፋፋዩ ህወሓት ተገዢ አይሆንም።

በስልት ከተጠቀምንበት ህወሓት ብዙ ሚሊዮኖች የሕዝብ ገንዘብ አውጥቶበት ያዘጋጀው ስልጠና ለራሱ ከሚሰጠው ጥቅም በላይ ለዲሞክራሲያዊ ኃይሎች የሚሰጠው ጠቀሜታ ይበልጣል። ለምሳሌ፣ ግንቦት 7 እነዚህን ስልጠናዎች የኢትዮጵያን ወጣት ለትግል ያላቸውን ዝግጁነት ለመገምገም ተጠቅሞበታል። “የኢትዮጵያ ወጣት ለትግል ዝግጁ ነው - የቀረው ድርጅት ነው” ሲል የግምገማውን ውጤት አሳውቋል። በዚህም ርዕሰ አንቀጽ ይህንኑ መልዕክት ማስረጽ ይፈልጋል።

በአምባገነን ሥርዓቶች ውስጥ የሚኖሩ ዲሞክራሲያዊ ድርጅቶች ከተለመዱ አደረጃጀቶች መለየት አለባቸው። መደበኛ (Formal) አደረጃጀቶች አባላትን ለአደጋ ያጋልጣሉ። በዚህም ምክንያት ነው ግንቦት 7፣ ኢ-መደበኛ (Non Formal) አደረጃጀቶች የሚመርጠው። በእኛ ሁኔታ “ኢ-መደበኛ አደረጃጀት” ስንል አራት ይሁን አምስት የሚተማመኑ ወጣቶች የሚፈጥሩት የግንቦት 7 ሴል ነው። ይህንን ሴል የፈለጉትን ስም ሊሰጡት ይችላሉ - እድር፣ ክበብ፣ የሆነ ስፓርት ቡድን ደጋፊ የተመቻቸውን ስያሜ ይስጡት። የተቋቋመበት ዓላማ ግን ግልጽ ነው - ለፍትህና ለነፃነት የሚደረገውን ትግል ማገዝ ነው። ይህ ኢ-መደበኛ ስብስብ ራሱን የግንቦት 7 አካል አድርጎ ይቁጠር። የግንቦት 7 ፕሮግራሞችንና ጽሁፎችን ያንብብ። ስብስቡ ለመረጃዎች ራሱን ቅርብ ያድርግ። መረጃዎችን ይለዋወጥ። በሂደት ቀጣዩ መንገድ ግልጽ እየሆነለት ይመጣል።

እየተካሄደ ያለው የህወሓት የጅምላ ስልጠና ለኢ-መደበኛ ድርጅቶች መስፋፋት ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል። የግንቦት 7 አባላትና ደጋፊዎች እነዚህን ስልጠናዎች የግንቦት 7 ሴሎችን ለማደራጀት እንዲጠቀሙበት እንመክራለን። ግንቦት 7 በኢትዮጵያ ወጣት የፈጠራ ችሎታ ላይ እምነት አለው። የኢትዮጵያ ወጣት አደንቁሮ ሊቀብረው የመጣውን ስልጠና ህወሓትን ለመቅበሪያነት እንደሚጠቀምበት የግንቦት 7 እምነት ነው።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

---

## ተማሪዎች ዘንድሮም ለአባይ ግድብ ማሰሪያ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

መንግስት ለአባይ ግድብ ማሰሪያ ከህዝብ እሰበስበዋለሁ ብሎ ያሰበው እቅዱ አልተሳካለትም። በአቶ ሃይለማርያም ደሳለኝና በአቶ በረከት ስምኦን የሚመራው የገንዘብ አሰባሳቢ ኮሚቴም እንቅስቃሴዎችን ሲያደርግ አይታይም። በውጭ አገር ለግድቡ ማሰሪያ ይደረጉ የነበሩ ዝግጅቶችም በውጭ አገር ከሚገኙ ኢትዮጵያውያን በሚደርሰው ተቃውሞ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ቆመዋል።

## የለውጡ አካል መሆኛው ግዜው አሁን ነው

እኔም አንዳርጋቸው ነኝ የሚል ድምፅ ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ እያሰተጋባ ነው። ይሄን ድምፅ የሚያቆመው አንዳችም ምድራዊ ኃይል አልተገኘም። ኢትዮጵያዊ ባለበት ሥፍራ ሁሉ ይሄ ድምፅ ከፍ ብሎ እየተሰማ ነው። ይህንንም ተከትሎ "ላንቺ ነው ኢትዮጵያ፤ ላንቺ ነው ኢትዮጵያ" የሚለው መዝሙር በኢትዮጵያ ተራሮች እናት ላይ እየተዘመረ ነው። ፍትህ ተዋርዳለች፤እኩልነት ጠፍቷል፤ ነፃነት የለም ያሉ ምርጥ ኢትዮጵያዊያን ሳያቅማሙ አያቶቻቸው በተመላለሱበት ተራሮች ላይ ተሠማርተዋል። ሞትንም ንቀው ጋሻ አንስተዋል፤ ሰይፋቸውንም መዘዋል። ለፍትህ፤ ለዕኩልነት እና ለነፃነት የተመዘዘው ሰይፍ ከእንግዲህ ወደ ሰገባው እንደማይመለስ ህወሃቶች እንዲያውቁት እንፈልጋለን።

በኢትዮጵያችን ፍትህ ከጠፋ ብዙ ዘመን ሁኖታል። ከሁሉም ዘመን የህወሃቶች ዘመን ግን የተለየ ነው። ህወሃቶች ህግን ዜጎችን የማጥቂያ መሣሪያ አድርገው መጠቀማቸው ከሌሎች እንዲለዩ ያደርጋቸዋል። እነዚህ ቡድኖች ሥፍር ቁጥር የሌላቸው ቂም መወጣጪያ ህጎችን አውጥተዋል። እንዲህ በማድርጋቸውም ሠላም እናገኛለን ብለው ያስባሉ። የህወሃቶች አስተሳሰብ ደካማና እርባና ቢስ መሆኑን ከሚያሳዩ ተግባሮቻቸው መካከል አንዱ ይሄው በፍትህ ሳይሆን በህግ ብዛት ሠላም እናገኛለን ብለው ተስፋ ማድረጋቸው ነው። የህግ ብዛት ሠላምን አያስገኝም፤ ፍትህንም ማስፈን አይችልም። እንዲያውም ህግ በበዛ ቁጥር ፍትህ እየጎደለች እንደምትሄድ የህወሃቶች ድርጊት ደህና ምስክር ነው። እነርሱ ዜጎችን ለመበቀያ ብለው የሚያወጧቸው ጥቃቅን ህጎች እነርሱ "ህገ መንግስት" ብለው የሚጠሩትን የሚንዱ እና ፍትህን ዋጋ የሚያሳጡ ሁነው እያየናቸው ነው። የፀረ ሽብር ህጉ በህገ መንግስቱ የተቀመጠውን የዜጎችን የመናገር የመደራጀትና በሰላማዊ መንገድ የመንግስትን እኩይ ተግባራት የመቃወምን መብት የገፈፈ ነው። የፀረ ሙስና ህጉም ቢሆን እንዲሁ ነው። በፀረ ሙስና ህጉ የሚጠየቁ በህወሃት የተጠሉ ብቻ ስለመሆናቸው በሙስና የተጨማለቁት የህወሃት ሹማምንት ህያው ምስክሮች ናቸው። በህወሃቶች ህግ ሁሉም ዜጎች እኩል አይደሉም። ህወሃቶች ከሌሎች ይበልጣሉ። የህወሃቶች ምኞት እነርሱ ከህግ በላይ፤ ሌላው ህዝብ ከህግ በታች ሁነው ህወሃትን ተሸክመው እንዲኖሩ ነው። እንዲህ ዓይነቱን ኢ-ፍትሃዊነት መታገል ግዜው የሚጠይቀው ታሪካዊ ግዴታ ነው። መሪያችን አንዳርጋቸው ፅጌ የተነሳውም ህወሃቶች መሣቂያ መሳለቂያ ያደረጓትን ፍትህ ወደ ሚገባት ክብር ለመመለስ ነው። በአገራችን የህግ የበላይነት ሠፍኖ ጥቂቱ ብዙሃኑን ሳይጫን፤ ማንም ማንንም ሳይሸከም ሁሉም በህግ እና በፍትህ እኩል ሁኖ የሚኖሩባት ሠላም የበዛላት ሥፍራ እንድትሆን የመሪያችን የአንዳርጋቸው ምኞት ነው። ይሄን ምኞት ሚሊየኖች አንግበው ተነስተዋል።

ህወሃቶች አገራችንን አደጋ ላይ ከጣሉባቸው አንኳር ድርጊቶቻቸው መካከል አንዱ በዜጎች መካከል እየፈጠሩ ያሉት ግልፅ ልዩነት ነው። ህወሃቶች ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር እኩል ነን የሚል እምነት የላቸውም። የህወሃቶች ዕምነት እነርሱ ከሌላው ኢትዮጵያዊ ከፍ እንደሚሉና በዚያች አገር ውስጥ የተለየ መብት እንዳላቸው ነው። ለመገድልም፤ ለመዝረፍም፤ዜጎችን ለማሳቃየት እና ከአገር ለማባረርም መብቱ የእኛ ነው የሚል ጅላጅል እምነት አላቸው። ይህ የሞኝ እምነታቸው በዜጎች መካከል ቂመ በቀል ሊያተርፍ የሚችል አድሎዎ እንዲፈጥሩ አድርጓቸዋል። አድሎአቸውንም ይበልጥ የከፋ የሚያደርገው ህወሃቶች ሁሉን አድራጊ እኛ ነን ብለው ሲያበቁ የህወሃት የበላይነት የለም ብላችሁ እምኑ ብለው ዜጎችን መጫናቸው ነው። ይህ ድርጊታቸው ብዙ ዜጎችን አስቆጥቷል። ህወሃቶች ግን የዜጎችን ቁጣ የሚያይ ዓይን፤ የሚያስተውል ሂሊና ርቋቸዋል። በኢትዮጵያችን በህወሃቶች አማካኝነት እየተፈጠረ ያለው ግልፅ አድልዖ ለአገራችን ህልውና ከፍተኛ አደጋ ነው። በህዝብ መካከል አድልዖ መፈፀም እና ቂምና በቀልን መትከል የህወሃቶች የመኖሪያ ድንኳናቸው ሁኗል። መከፋፈልና አድልዖ ባለበት አገር ውስጥ ሠላም ይኖራል ማለት አይቻልም። አድልዎ የታላላቅ ግጭቶችና ለውጦች ጥሩ ምክንያት መሆኑን መርሳት አይገባንም።መሪያችን አንዳርጋቸውም ሆነ ግንቦት ሰባት ንቅናቄ የተነሳው እንዲህ በዜጎች መካከል የሚፈፀመውን አድልዖ ለማስቆምና ዜጎች በገዛ አገራቸው በእኩልነት የሚኖሩበትን ሁኔታ ለመፍጠር ነው። ይህ የእኩልነት ጥያቄ የግንቦት ሰባት ንቅናቄ ብቻ ሳይሆን የሁሉም ዜጎች ጥያቄ ሁኖ ከኢትዮጵያ እስከ ውጪ አገራት ድረስ እያስተጋባ ነው።

ሌላው ህወሃቶች አገሪቷን እያዋረዱ ካሉበት ነገሮች መካከል አንዱ የነፃነት ጥያቄ ነው። እኛ ከመጣን በኋላ በኢትዮጵያ ነፃነት ሰፈነ እያሉ ያላዝናሉ። ህወሃቶች ከነፃነት ጋር ተያይዞ ሊመጣ የሚችለውን ኃላፊነት ለመረዳትና ለመሸከም ከፍተኛ የሆነ የአስተሳሰብ ድክመት አለባቸው። ከነፃነት ጋር የሚመጣውን ኃላፊነት ለመሸከም ብቻ ሳይሆን የነፃነትንም ትርጉም ለመረዳት ከፍተኛ የሆነ የእውቀት ማነስ ችግር ያለባቸው መሆኑም ይታወቃል። ራሳቸውን ከታሰሩበት የድንቁርና ሰንሰለት ማስፈታት ሳይችሉ ከሰሞኑ የከፍተኛ ተቋም ተማሪዎችን ሰብስበው የእኛን አብዮታዊ ዲሞክራሲ ካልስተማርናችሁ ትምህርታችሁን አትቀጥሉም ሲሉ ማሰብ ማቆማቸውን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳየን አንድ እውነት ሁኖ አግኝተነዋል። ማሰብ የሚችሉ ቢሆኑማ ኑሮ ነፃነት ማለት *'የእናንተን አብዮታዊ ዲሞክራሲ መስማት አልፈልግም ማለትን'* እንደሚጨምር ያውቁ ነበር። ነፃነትን የማያውቁት ነፃ አውጪዎች ነን ባዮቹ ህወሃቶች ግን ተማሪው መስማት የማይፈልገውን አብዮታዊ ዲሞክራሲ አስገድደው እየጋቱት ይገኛሉ። ለሚቀጥለውም አርባና ሃምሳ ዓመት ስልጣኑን ለማንም አሳልፈን የምንሰጥ አይደለንም ሲሉ በድፍረት ተናግረዋል። የዚህ ሁሉ ድፍረት ምንጭ ህወሃቶችን የተፀናወታቸው እኔ ብቻ ከሚል ከንቱ አስተሳሰብ የመነጨው ስግብግብነታቸው መሆኑን መገነዘብ ያስፈልጋል።

እንግዲህፍትህ መቀለጃ ሁናለች፤ እኩልነት ተጓድሏል፤ ነፃነት ጠፍቷል የሚሉ ዜጎች ከሁሉም አቅጣጫዎች ድምፃቸውን እያሰሙ ነው። የህዝቡ ብሶትም ፅዋውን ሞልቶ እየፈሰሰ ነው፤ ቁጭቱም ከመቸውም ግዜ በላይ ግሏል። ከሰሞኑ በሃያ ስድስት ታላላቅ ከተሞች የተደረጉት ውይይቶችም ያሳዩን አንድ እውነት ህዝቡ ይበልጥ መቆጣቱን ነው። ቁጣውም የተገለፀበት መንገድም ሌላው አስደማሚ ጉዳይ ነው።*"እኛም አንዳርጋቸው ነን"* ሲሉ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው አሰምተዋል። ከእንግዲህ ፍርሃት ሆይ መወጊያህ ወዴት አለ የሚሉ ኢትዮጵያዊያን ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ላንቺ ነው ኢትዮጵያ፤ ላንቺ ነው ኢትዮጵያ እያሉ ዘምረዋል። ይሄ ለፍትህ፤ ለእኩልነትና ለነፃነት ለሚታገሉ ታጋዮች ተስፋ ሰጪ ምልክት ነው።

ህወሃቶች በሠላማዊ መንገድ ለሚደረገው ትግል መንገዱን ሲያደናቅፉ እስከ ዛሬ ዘልቀዋል። አሁን ጭራሹን ገና ሃምሳ የመከራ ዘመን እየተመኙልን ነው። ይሄ ምኞታቸው ቅዥት ሁኖ እንደሚቀር እኛ ልናስታውሳቸው እንፈልጋለን። በዚያች አገር ለውጥ መምጣት አለበት። ለውጡ በዛፍ ላይ የተንጠለጠለ የጎመራ ፓፓያ አይደለም በራሱ ወደ ምድር የሚወርድ፤እኛ ራሳችን ልናወርደው የሚገባን እንጂ። ተፈላጊውን ለውጥ ለማምጣት እያንዳንዱ ዜጋ በቻለው መሣሪያና ባለው አቅም ሁሉ ለልውጡ ሳያቅማማ መታገል ይኖርበታል። ህወሃቶች ነፃነታችንን አይሰጡንም፤ ፍትህም ከእነርሱ እጅ የምትገኝ አይደለችም፤ እኩልነትንም የሚያውቁ አይደሉም እነዚህ ወርቃማ እሴቶች በትግል የሚገኙ ናቸው። እነዚህን ክቡር ስጦታዎች አስነጥቆ ዝም ያለ ወደ መታረጃው ሥፍራ የሚነዳ ከብትን ይመስላል። ብዙ ኢትዮጵያዊያን እንዲህ መሆንን የሚምርጡ አይደሉም። በየከተሞቹ በተደረገው ውይይት ከተገነዘብናቸው እውነቶች መካከል አንዱ ዜጎች ለፍትህ፤ለእኩልነት እና ለነፃነት አስፈላጊውን መሥዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ መሆናቸውን ነው።

በህወሃት ዘመነ መንግስት የመከራ እንባችሁን በመዳፋችሁ የምታፍሱ፤ ህወሃት በአገሪቷ ላይ እያደረሰ ያለው የጥፋት ድርጊት የሚያነገበግባችሁ እና ምን እናድርግ መሪ አጣን የምትሉ ስሙን! መሪ ካጣችሁ እንዲህ አድርጉ "ራሳችሁ ተነሱና መሪ ሁኑ!"። ከምታምኗቸው ጥቂት ወዳጆቻችሁ ጋር ሁናችሁ ተደራጁ፤ አንዳችሁ አንዳችሁን አድምጡ፤ ጥሩ ተመሪ መሆን ከቻላችሁ ጥሩ መሪ ወጥቷችኋል ማለት ነው። የአገራችን ፈርጀ ብዙ ችግር በጥቂት ዜጎች ብቻ የሚቀረፍ አይደለም።የሁሉንም ቁርጠኛ ዜጎች ትግል የሚጠይቅ ነውና በየመንደራችሁ ተደራጅታችሁ የጎበዝ አለቃ መርጣችሁ ዘረኞችን፤ ዘራፊዎችንና አድሎዋዊ ሥርዓት የዘረጉባችሁን ታገሏቸው። እንዲህ ካደረጋችሁ ከእኛ ጋር ለመገናኘት መንገዱ ቀላል ይሆናል።

የግንቦት ሰባት ንቅናቄ ጥያቄ አጭርና ግልፅ ነው። ፍትህ፤ ነፃነትና እኩልነት በኢትዮጵያችን ይሰፈን ነው። የህወሃትን ዘረኝነትና አምባገነንነት የሚፀየፍ ሁሉ የንቅናቄያችን ደጋፊ ነው። እነዚህን ነገሮች በኢትዮጵያ ለማስፈን በሚችለው ሁሉ ርምጃ መውሰድ የጀመረ የንቅናቄያችን አካል ነው። እኛም ከጎኑ አለን። እንዲህ በማድረግ የማይቀረውን ለውጥ አናመጣለን። ለውጡ ይመጣል አንድም የተፈጥሮ ህግ ስለሆነ፤ አንድም ደግሞ እኛ ሳናቅማማ የፈለግነውን ለውጥ ለማምጣት ስለተነሳን።

ህወሃቶች መስልጠን የማይችሉ፤ ከአዲስ አስተሳሰብ ጋር ራሳቸውን ማዋሃድ የማይሆንላቸው ፍፁም ግትሮች መሆናቸውን በተዳዳጋሚ አይተናል። ይሄን ግትርነታቸውን እንደ ጀግንነት ይቆጥሩታል። በአገራችን ደህና አባባል አለች እንዲህ የምትል "ሞኝ አሸነፈ ምን ብሎ? እምቢ ብሎ" ይባላል። ህወሃቶችን በዚህ አባባል መግለፅ ሞኝ ያስመስላቸዋል እነርሱ ግን ሞኞች አይደሉም ጨካኞች እንጂ። የጭካኔያቸው ምንጭ ደግሞ በራሳቸው የማይተማመኑ ደካሞች መሆናቸው ነው። እነርሱ ከዛሬ ሠላሳ ዓመት በፊት በመስታወት ውስጥ ያዩትን የራሳቸውን ምሥል ዛሬም መልሰው ያንኑ ምሥል እያዩት ነው። ከሠላሳ ዓመት በኋላም ሊቀየሩ አልቻሉም። ከዚያ ካረጀው ምሥላቸው ላይ ዓይናቸውን ነቅለው ግዜው እና ሁኔታው የፈጠረውን በአካባቢያቸው ያለውን አዲስ ምሥል ለማየት አቅቷቸውል። ስለዚህ ህወሃቶችን ማስወገድ ግድ ነውና ሁሉም በያለበት ለሚመጣው ለውጥ ራሱን ያዘጋጅ፤ የለውጡም አካል ይሁን እንላለን።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!**

## የወያኔ መሪዎችና ያፈናቀሏቸዉ የውቤ በረሃ ተፈናቃዮች አሁንም እንደተፋጠጡ መሆኑ ተሰማ

አዲስ አበባ ዉስጥ በአራዳ ክፍለ ከተማ ከጊዮርጊስ ወደ አፍንጮ በር በሚወስደው መንገድ ላይ የሚገኘው የውቤ በረሃ ነዋሪዎች፣ የክፍለ ከተማው አስተዳደር የገባልንን ቃል ባለመፈጸሙ ዕጣ አውጡና አራት ኪሎና ልደታ ከተገነቡ የኮንዶሚኒየም ቤቶች አንደኛዉ ይደርሳችኋል የሚለውን የአስተዳደሩን ጥያቄ ውድቅ አድርገዉ ከክፍለ ከተማው አስተዳደር ጋር ፊት ለፊት መፋጠጣቸዉን አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ ዘጋቢዎቻችን በላኩልን ዜና ገለጹ። ከአንድ ዓመት በፊት ከ514 በላይ አባወራዎችን በሀገር ፍቅር ቴአትር ቤት የክፍለ ከተማው አስተዳደርና የወረዳዎቹ ተወካዮች ሰብስበዋቸው ቦታው ለልማት እንደሚያስፈልግ ሲነግሯቸው፣ አራት ኪሎና ልደታ ከተገነቡ የኮንዶሚኒየም ቤቶች በዕጣ እንደሚሰጣቸው ቃል ተገብቶላቸው እንደነበር ነዋሪዎቹ ያስታውሳሉ።

በመሆኑም ኮሚቴ በማቋቋም ከዓመት በላይ ጉዳዩን ሲከታተሉ ቆይተው ሰሞኑን ዕጣ ማውጣት እንዳለባቸው ተነግሯቸው ሲሄዱ፣ ዕጣ የሚያወጡት ለአራት ኪሎና በልደታ ሳይሆን ገላን ለተገነቡ የኮንዶሚኒየም ቤቶች መሆኑን ሲያውቁ፣ «ዕጣ አናወጣም» በማለት መቃወማቸውን ገልጸዋል።ነዋሪዎቹ እንደገለጹት፣ ነሐሴ 25 ቀን 2006 ዓ.ም. በቅድሚያ አቅመ ደካማ ለሆኑ 35 አባወራዎች ዕጣ ሲያወጡ ሳይቱን ማየታቸውንና «የተገባልን ቃል ከአካባቢያችሁ ሳትርቁ በቅርብ ባሉ ኮንዶሚኒየም ቤቶች ትገባላችሁ የሚል ነው፤» በማለት አስተዳደሩን መቃወማቸውን ተናግረዋል።

«እኛ ጥያቄያችን የፖለቲካ አይደለም። እኛም ሆንን ልጆቻችን ሰላም ፈላጊዎች ነን፤» የሚሉት ነዋሪዎቹ፣ ዓመቱን ሙሉ በአግባቡ እየተሰበሰቡና ከወረዳው አመራሮች ጋር ሲመካከሩ ቆይተው፣ ቅድሚያ ለፈረሰባቸው 50 ነዋሪዎች ጀሞ ሳይት ቤት ሰጥተው ሲያስገቡ፣ «የቅርቡ ሳይት ስላልደረሰልን ነው» በማለት አታለዋቸው፣ አሁን ደግሞ እነሱን «ገላን ሳይት ትገባላችሁ» በማለት ወደ አመፅና ሁከት ለማስገባት የሚደረገውን ጥረት እንደሚቃወሙ አስታውቀዋል።ከ217 በላይ አባወራዎች (አብዛኛዎቹ አዛውንቶች ናቸው) የከተማውን ከንቲባ ለማነጋገር ጥረት ሲያደርጉ ለነሐሴ 26 ቀን 2006 ዓ.ም. የተቀጠሩ ቢሆንም፣ በዕለቱ ሊያነጋግሯቸው አለመቻላቸውን ነዋሪዎቹ ገልጸው፣ አሁንም የሚጠይቁት ከዓመት በፊት በተገባላቸው ቃል መሠረት በቅርቡ በተገነቡ አራት ኪሎና ልደታ ሳይቶች ዕጣ እንዲወጣላቸው መሆኑን አስረድተዋል።

በገላን ሳይት ከዚህ ቀደም የፈረንሳይ ነዋሪዎች እንዲገቡ ተጠይቀው «አንቀበልም» ማለታቸውን የገለጹት ነዋሪዎቹ፣ ከስምንተኛ ክፍል በላይ ትምህርት ቤት ሳይኖርና በቂ ጤና ጣቢያ እንኳን በሌለበት አካባቢ እንዲገቡ ማስገደድ ተገቢ አለመሆኑን ተናግረዋል። አስተዳደሩ በገባላቸው ቃል መሠረት ሊፈጽምላቸው እንደሚገባም አክለዋል። የወረዳው አስተዳደር ነዋሪዎቹን በመከፋፈልና ልጆቻቸውም በማያውቁት የፖለቲካ ድርጅት «አባል ናችሁ» በማለት ለማስፈራራት ጥረት በማድረግ ላይ መሆኑን ጠቁመው፣ «ይኼ ለማንም አይበጅም፣ ልጆቻችንም ሆኑ እኛ የምንፈልገው መብታችን እንዲከበር ብቻ ነው፤» ብለዋል።

## በምርጫ 97 በግፍ ለተገደሉ ዜጎች ካሳ የሚያስከፍል ክስ ሊመሰረት ነዉ

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ በ1997 ምርጫ ወቅት በግፍ ለጨፈጨፋቸዉ 200 ሰዎችና በመቶዎች ለሚቀጠሩ ቁስለኞች የወያኔን መሪዎች ተጠያቂ የሚያደርግና በዚያዉም ለደረሰዉ ጉዳት ተመጣጣኝ ከሳ የሚያስከፍል ክስ በወያኔ አገዛዝ ላይ እንደሚመሰርቱ አንድ ሲዉዲናዊ የህግ ባለሙያ አሳዉቁ።

ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት እና ወታደራዊ አዛዦች ላይ ለፖሊስ የክስ አቤቱታ ያስገቡት ታዋቂዉ ስዊድናዊ የህግ ከኢሳት ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ፣ በቅርቡ ለፖሊስ ከገባው አቤቱታ በተጨማሪ የኢትዮጵያ መንግስት በግፍ ለተገደሉት፣ ለቆሰሉት ፣ ለታሰሩት፣ ከስራ ለተፈናቀሉት አስፈላጊውን ካሳ እንዲከፍል ለማስገደድ የገንዘብ ማሰባሰብ ስራ እየሰሩ መሆኑን ገልጸዋል። አብዛኛውን የምርመራ ስራ የሚሰራውና ወጪውን የሚሸፍነው የስዊድን ፖሊስ ቢሆንም፣ ምስክሮችን ለማስመጣትና ተጨማሪ ሰነዶችን ለማሰባሰብ ገንዘብ እንደሚያስፈልግም ተናግረዋል።

ገንዘብ የሚያስፈልገው ክሱን ለሚመሰርቱት የህግ ባለሙያዎች አይደለም የሚሉት ስቴላ፣ በክርክሩ ወቅት የኢትዮጵያ መንግስት ቢያሸንፍ፣ መንግስት ለሚያቆመው ጠበቃ ወጪ መክፈል ስላለበትና ወጪውን የሚሸፍነውም የተረታው አካል በመሆኑ ነው ብለዋል። የኢትዮጵያ መንግስት በክሱ ከተረታ ግን በውጭ ያለው ሃብቱ ታግዶ ለተጎጂዎች እንዲሰጠጥ ይደረጋል ብለዋል።በ13 የመንግስት ባለስልጣናት ላይ የክስ አቤቱታ ቢቀርብም በመንግስት ላይ እስካሁን አልቀረበም ያሉት ስቴላ፣ ኢትዮጵያውያን አስፈላጊውን መዋጪ ማድረግ ከቻሉና በቂ ገንዘብ እንዳለ ሲታወቅ የካሳ መጠየቂያ ክሱ ወዲያው ይከፈታል ብለዋል። ማንኛውም ገንዘብ አለማቀፍ ደረጃ ባላቸው የሂሳብ ሰራተኞች እንደሚታይና የተዋጣው ገንዘብ ለህዝብ ይፋ እንደሚሆን ገልጸዋል።

ሰሞኑን ለፖሊስ የቀረበውን አቤቱታ በተመለከተ ጥያቄ የቀረበላቸው ስቴላ፣ ፖሊስ ማመልከቻውን ተቀብሎ ምርመራ መጀመሩንና በሁለት ወይም ሶስት ሳምንታት ውስጥ ለስዊድን አለማቀፍ ወንጀል አቃቢህግ እንደሚያስተላልፍ ተናግረዋል። አቃቢ ህግ የቀረቡትን መረጃዎች አይቶ ክሱን ወደ ፍርድ ቤት ለመውሰድ ወይም ላለመውሰድ እንደሚወስን የገለጹት ስቴላ፣ የቀረቡት ማስረጃዎች ክሱ በአጭር ይቋጫል ብለው ለመናገር እንደማያስድፈራቸው ገልጸዋል። ከአለፉት አስር አመታት ወዲህ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች እና የጦር ወንጀሎች በየትኛውም አገር መታየት መጀመራቸው ክሱን ለመመስረት እንዳነሳሳቸው ጠበቃው ገልጸዋል። አቃቢ ህግ ክስ ለመመስረት ከወሰነ ስዊድን ውስጥ ያሉ ተጠያቂዎች በቁጥጥር ስር እንደሚውሉ፣ ሌሎች ከስዊድን ውጭ የሚኖሩ ባለስልጣናት ደግሞ በኢንተርፖል በኩል ስማቸው ተላልፎ ተይዘው ክሳቸውን እንዲከታተሉ እንደሚደረግ አክለው ገልጸዋል።

## ከኢትዮጵያ የሚሰደዱ ጋዜጠኞች ቁጥር እየጨመረ ነዉ

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ የሚቃወሙትን ሀይሎች በሙሉ እንዳሰኘዉ ማጥቃት የሚያስችለዉን የጸረ ሽብር ህግ ካወጣ በኋላ አያሌ ሰላማዊ ጋዜጠኞችና የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች ሽብርተኞች እየተባሉ ሃያ አምስት አመትና ዕድሜ ለክ እስራት እየተፈረደባቸዉ ቃሊቲ መዉረዳቸዉ የሚታወቅ ነዉ። ይህ የወያኔ የግፍ አስርና ቅጣት ቀድሞዉንም በአንድ እግሩ የሚንገዳገደዉን የግሉን ፕሬስ ሞቶ እንዲቀበር አድርጎታል። ወያኔ ያወጣዉን የሽብር ህግ ተገን በማድረግ በጋዜጠኞች ላይ የተከፈተውን ዘመቻ ተከትሎ፣ አገር ጥለው የሚወጡ የነጻው ፕሬስ አባላት ቁጥር መጨመሩንም የተለያዩ መረጃዎች አመልክተዋል።

ባለፉት ሁለት ሳምንታት ከ12 ያላነሱ ጋዜጠኞች ከደህንነት ሃይሎች በደረሰባቸው ጫና ምክንያት አገራቸውን ጥለው የተሰደዱ ሲሆን፣ ብዙዎቹ በስደትበሚኖሩባቸው አገሮች ለችግር ተዳርገዋል። የኢትዮጵያ የደህንነት ሃይሎች ያለ ተቆጣጣሪ ገብተው በሚወጡባት ኬንያ የሚገኙ ጋዜጠኞች በስጋት ውስጥ መሆናቸውን ኢሳት ያነጋገራቸው ጋዜጠኞች ገልጸዋል። ባለፉት 2 ቀናት የተሰደደውን፣ በተለያዩ መጽሄቶች ላይ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ይዘት ያላቸውን ጽሁፎች በመጻፍ የሚታወቀው ጋዜጠኛ ብስራት ወ/ሚካኤልን ጨምሮ ጋዜጠኛ በትረ ያዕቆብ፣ ተሰማ ደሳለኝ፣ ዘሪሁን ሙሉጌታ፣ መላኩ አማረ፣ ግዛው ታየ፣ ቶማስ አያሌው፣ ሰብለወርቅ መከተ፣ አቦነሽ አበራ፣ ሰናይ አባተ፣ አስናቀ ልባዊ፣ ሲሳይ ሳይሌ፣ እንዳልካቸው ተስፋየ፣ ኢብራሂም ሻፊ፣ እንዳለ ተሺ፣ ሀብታሙ ስዩም፣ ዳዊት ሰሎሞንናዳንኤል ድርሻ የተባሉ ጋዜጠኞችና አሳታሚዎች ተሰደዋል። ጋዜጠኛ በትረ ያእቆብ፣ ብስራት ወ/ሚካኤልና ዘሪሁን ተስፋየ በቅርቡ የተቋቋመውየኢትዮጵያ ጋዜጠኞች ህብረት ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንትና የህዝብ ግንኙነት ሃላፊ በመሆን ሰርተዋል።

የተሰደዱት ጋዜጠኞች ኢቦኒ፣ ሰንደቅ፣ ሊያ፣ ሎሚ፣ አፍሮ ታይምስ፣ ጃኖ፣ ፒያሳና አዲስ ጉዳይ በተሰኙት መጽሄቶች ላይ ሰርተዋል።መንግስት በጋዜጦች ላይ የሚወስደው እርምጃ ከመጪውን ምርጫ ጋር የተያያዘ ነው በሚል ይተቻል። ዞን ዘጠኝ እየተባሉ የሚጠሩ በማህበራዊ ድረገጾች ላይ የሚሳተፉ ጸሃፊዎች እንዲሁም በተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ ጉልህ ስፍራ የነበራቸው ሃብታሙ አያሌው፣ አብርሃ ደስታ፣ የሽዋስ አሰፋና ዳንኤል ሽበሺ መታሰራቸው ገዢው ፓርቲ መጪውን ምርጫ ያለምንም ችግር ለመለፍ የወሰደው እርምጃ ነው በማለት የፖለቲካ ድርጅቶች መግለጻቸው ይታወሳል።ከዚሁ ጋር በተያያዘ የአውሮፓ ህብረት በኢትዮጵያን ውስጥ ስላለው የሰብአዊ መብት ጥሰትና ዲሞክራሲ ሁኔታ ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር አለመስማማታቸውንሪፖርተር ዘግቧል።ጋዜጣው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ ዲና ሙፍቲን ጠቅሶ እንደዘገበው፣ የህብረቱ አባላት አቶ ሃይለማርያም ደሳለኝን ጨምሮ ሌሎች የመንግስት ባለስልጣናት በተገኙበት በኢኮኖሚ፣ በንግድ፣ በኢንቨስትመንት እና ተያያዥ ጉዳዮች ውይይት ሲያደርጉ በሰብአዊ መብት አያያዝ ላይ ስምምነት ላይ ሳይደርሱ ቀርተዋል። መንግስት ከአውሮፓ ህብረት የቀረበውን ትችት ሳይቀበለው መቅረቱንም ባለስልጣኑ ገልጸዋል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
<u>አጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## የግንቦት 7 የፍትህ፤ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ አለማቀፍ ህዝባዊ ስብሰባዎች . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ተቀናብረው ለእይታ የቀረቡ ሲሆን የነፃነት አርበኛው የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ስራዎችና አሁን ላይ በጠላት እጅ መውደቃቸው ኢትዮጵያውያኑን በቁጭት አስነብቷል፤ በበለጠ ትግሉ ለሚጠይቀው ማንኛውም መስዋዕትነት በእልህና በቁጣ ያነሳሱዋቸው እንደነበሩም ለማወቅ ተችሏል።

ኢትዮጵያውያኑ ፋሽስቱ ወያኔን ማስወገድ በሚቻልባቸው የትግል ስልቶች ላይ ሰፊ ውይይት ከድርጅቱ አመራሮች ጋር ያደረጉ ሲሆን ኢትዮጵያውያኑ በንቅናቄው የተነደፉትን የትግል ስሎች በማድነቅ ወደፊትም የጉጅሌው ወያኔን በመገርሰስ ትግሉን ከዳር ለማድረስ ለሚጠይቃቸው ማንኛውም አይነት መስዋዕትነት ዝግጁ መሆናቸውን አረጋግጠዋል፤ ኢትዮጵያውያኑ በአንድነት እጅ ለእጅ በመያያዝም ትግሉን ከዳር ለማድረስ ቃል ኪዳን መግባታቸው ተዘግቧል። ትግሉን ከዳር ለማድረስ በገንዘብ፤ በሰው ሃይልና በዕውቀት ረገድ ድጋፍ በማድረግ ከንቅናቄው ጎን እንደሚሰለፉ ቃል መግባታቸውንም ዘጋቢዎቻችን አመልክተዋል። በቅርቡ የተሰማው ውህደትን የተመለከተው የብስራት ዜና ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበትና ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ተቀራርቦ በጋራ መስራት የሚቻልበት ሁኔታዎች መመቻቸት እንዳለበት ኢትዮጵያውያኑ ማሳሰባቸው ታውቋል።

በመጨረሻም የነፃነት ትግሉ የደረሰበትን ደረጃ በተመለከተ ሰፊ ማብራሪያ የሰጡት የድርጅቱ ከፍተኛ አመራሮች አሁን ወሳኝ የትግል ምዕራፍ ላይ ደርሰናልና ሁሉም አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ በአንድነት ልንረባረብ ይገባል በማለት ኑ! ኢትዮጵያ አገራችንን፣ ኢትዮጵያዊ ወገናችንን እና ራሳችን ነፃ ለማውጣት እና በሀገራችን ፍትህና ዲሞክራሲ እንዲሰፍን ለማድረግ በምናደርገው ትግል ተቀላቀሉን ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል። ለቀረበውን አገር አድን ጥሪ ምላሽ በመስጠት በሁሉም የህዝባዊው ስብሰባ ቦታዎች ላይ በርካታ ኢትዮጵያውያን በትግሉ ለማሳተፍ በአባልነትና ደጋፊነት አስተዋፅኦ ለማበርከት መመዝገባቸውንም ለማወቅ ተችሏል። በተጨማሪም በአገር ውስጥና በውጭ አገር ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች፤ እና ለኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት አባላት የጉጅሌው ወያኔን አገዛዝ ለማስወገድ እየተደረገ ያለውን የሞት ሽረት ትግል እንዲቀላቀሉ ጥሪ መቅረቡንም ለማወቅ ተችሏል።

## የኢህአዴግ አባላት በድርጅታቸው ላይ ጥያቄዎችን . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በታችኛው ህብረተሰብ አካባቢ በብልሹ አሰራር ውስጥ ገብተው ከፍተኛ ሙስና የሰሩና በህዝቡ የተገለሉ ሰዎች ተሸፍነው ወደ ላይ ሲወጡ ሹመት ይደረብላቸዋል ይህ ተገቢ ነወይ?" የሚሉ ጥያቄዎችም ተነስተዋል። የአዲስ አበባ የመሬት ወረራ ጉዳይም ሰፊ አጀንዳ የነበረ ሲሆን፣ ኢህአዴግ በሰላማዊና ጠንካራ ተቃዋሚዎች ላይ የያዘው አቋምም ትችት አዘል ጥያቄ አስነስቶበታል። የዛሬውን የፕላዝማ ውይይት የአዲስ አበባ ምክትል ከንቲባ አቶ አባተ ስጦታው መርተውታል። ትናንት ከሰአት በኋላ በነበረው የውይይት ጊዜ ደግሞ" ኢህአዴግ ለሃገሪቱ ስጋት ብሎ ከለያቸው የፖለቲካ ጉዳዮች ውስጥ ዋነኛ ያላቸው የሃይማኖት አክራሪነት ወይም ጽንፈኝነት እና የመልካም አስተዳደር እጦት ቢሆኑም፣ የኑሮ ውድነቱ በስጋትነት ሊካተት ይገባል" የሚል አስተያየት ቀርቧል የደመወዝ ጭማሪው አርኪ አለመሆኑና እንዳውም የበለጠ ህዝቡን ናየመንግስት ሰራተኛውን ለችግር መዳረጉም በአባላቱ ተነስቷል ሰልጣኞቹን በሚሰለጥኑበት ቦታ ጥያቄዎች ሲነሱ እዚያው በህዋሳቸው በሰልጣኞቹ እንዲመለስ በማሰብበህ ዋስ ማደራጀት መጀመሩን፣ ሰልጣኞቹ የመድረኩን የፕሮፓጋንዳ ገለፃ ብዙ ትኩረት ሳይሰጡ የጥያቄና መልስ ክፍለ ጊዜ ሲደርስ ግን በንቃትጥያቄየሚያነሱ ሲሆን፣ አንዳንዳ ጥያቄዎችን ከውይይሩ ጋር ግንኙነት የላቸውም ወይም ጥያቄውን ወደኋላ ላይ ማንሳት ትችላላችሁ በሚል እንደሚታለፉ የውስጥ ምንጮች ገልጸዋል።

ዘግይቶ በደረሰን ዜና ደግሞ የግንቦት 7 ድርጅት አጀንዳ የነበረ ሲሆን በአንዳንድ አባላት ዘንድ ግንቦት 7 ከውጭ መንግስታት ጋር በማበር አገር ዉስጥ አብዮት እንዲነሳ እየሰራ ነው ሲሉ ሌሎች አባላት ደግሞ ግንቦት 7 አሸባሪ ከተባለ ለምን የአሜሪካ መንግስትአሳልፎአይሰጥም? እናንተ እንደምትሉት አሸባሪ ቢሆን ኖሮ ያስሩዋቸው ነበር ብለው ተከራክረዋል። አወያዮቹም ከአሸባሪዎች ጋር መገናኘት የለባችሁም በሀገር የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚዎች አብረው እየሰሩ እንደሆነ ለአባላቱ የገለጹ ሲሆን ንክኪ እንዳይኖራችሁ ሲሉ አስጠንቅቀዋል።

በኢህአዴግ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የታየው ግምገማ መነሻ፣ በቅርቡ ኢህአዴግ መዳከሙን የተመለከተ ግምገማ ከተደረሰ በሁዋላ ነው። ይህን ተከትሎ ለዩኒቨርስቲ ተማሪዎች፣ ፖሊሶች፣ የህግ ባለሙያዎች በመንግስት ፖሊሲ ዙሪያ ስልጠና ሲሰጥ ቆይቷል። በስልጠናው ላይ የተነሱትን ጥያቄዎች የኢህአዴግ አባላት እንዲመክቷቸው በሚል እየተሰጠ ያለው ስልጠና ያልተጠበቁ ጥያቄዎችን ማስነሳቱ፣ ከፍተኛ አመራሮችን ሳይቀር በእጅጉ ማስገረሙን ምንጮች አክለው ገልጸዋል። "እዚህ የምናደርገው ስብሰባ በኢሳት ይዘገባል ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ ? "በሚል አመራሩ እየተነጋገረበት መሆኑንም ታውቋል። ብአዴንም መረጃዎች እየወጡ ተቸግረናል በሚል ትናንት በጀመረው ግምገማ ማንም ሰው ሞባይል ስልኮችን ይዞ እንዳይገባ ከልክሏል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ኢህአዴግ በአዲስ አበባ የሚገኙ መላ አባላቱን ለስልጠና ምቹ የሆኑ አዳራሾች ባሉዋቸው ትምህርትቤቶችና የመንግስት ተቋማት ዉስጥ ስብስቦ በፕላዝማ የታጀበ ስልጠና እየሰጠ ነው። ስልጠናው በመላው አገሪቱ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ያነሱዋቸው አፍራሽ የተባሉ ጥያቄዎች እና አመለካከቶች ወደ ህዝቡ ወርደው አደጋ ከመፍጠራቸው በፊት የኢህአዴግ አባላት እንዴት እንደሚከላከሉዋቸው ስልጠና ለመስጠት ያለመ ቢሆንም፣ የድርጅቱ አባላት ግን የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ያነሱዋቸውን ጥያቄዎች ደግመው እስከመጠየቅ በመድረሳቸው የድርጀቱ አመራሮች አባላት ያልሆኑ ሰዎች በስልጠናው ላይ ተገኝተዋልና እናጣራለን ብለው እስከመናገር መድረሳቸውን በስልጠናው ላይ የሚሳተፉ አባላት ለኢሳት ገልጸዋል።

የመጀመሪያው ቀን ስልጠና የተሰጠው በኢህአዴግ የጽ/ቤት ሃላፊና በከንቲባው ልዩ አማካሪ በሆኑት በአቶ ተወልዴ ወ/ጻድቅ ሲሆን፣ ከተለያዩ የስልጠና ቦታዎች የተነሱትን ጥያቄዎች በማንሳት መልስ ለመስጠት ሞክረዋል። በአባላቱ ዘንድ ከተነሱት ጥያቄዎች መካከል፣ ስለድሮ ታሪኮች መጥፎ መጥፎንውን ብቻ ለምን ትነግሩናላችሁ? ውይይቱ ስለኢህአዴግ ጥንካሬና ድክመት ብቻ ቢሆን እንመርጣለን፣ ሚኒሊክ አገርን አንድ ያደረገ የመጀመሪያው መሪ ሆኖ ሳለ ለምን ሁሌ በመጥፎ ይነሳል፣ አማራንና ኦሮሞን ለማጣላት ሆን ብላችሁ ታሪክ እያጣመማችሁ ነው፣ እናንተ ሳትማሩ እኛን የማሰልጠን ብቃት አላችሁ ወይ፣ ኤርትራን ያስገነጠላችሁት እናንተ እንጅ ሚኒሊክ አይደለም፣ ደርግ ኢትዮጵያ ትቅደም ይል ነበር እናንተ ደግሞ ዘር ይቅደም ትላላችሁ፣ አገሪቱን ከፋፍላችሁ ለምን የቀድሞ ስርዓት ከፋፈለው ትላላችሁ፣ ታሪክን እኛ እናንብብ እንጅ እናንተ አታስተምሩን፣ የአንድ ዘር የበላይነት ነግሷል፣ የአሰብን ወደብ እንድናጣ አድርጋችሁዋል፣ አማራን ተሳድባችሁዋል፣ የሚሉትና ሌሎችም ይገኙበታል።

አሰልጣኙ ኢህአዴግ እንደ ድርጅት ይህን አልተናገረም፣ ይህ አስተሳሰብና ጥያቄ በእኛ ውስጥ የለም፣ በየመጽሄቶችና ጋዜጦች ላይ የተለያዩ ሃይሎች የሚያቀርቡት ውንጀላ ነው የሚል መልስ ከመስጠትና የምትጠይቁት ጥያቄ ከአንድ አባል አይጠበቅም በማለት ከመናገር ውጭ ለተነሱት ጥያቄዎች የቀጥታ መልስ አለመስጠታቸውን አባላቱ ተናግረዋል። አባል ያለሆኑ ሰዎች በስልጠናው ላይ ተገኝተው ይሆናል በሚል ማጣራሪያ እንደሚደረግም አሰልጣኙ ገልጸዋል።